# ስንብት - ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት!

ጂቱ ለሚ

የካቲት 15 ቀን 2015ዓም

ያ ሰው በጣም ደስተኛ ነበር፡ ዛሬም ብዙዎች በየቀኑና በየቦታው 26ቱን ማይልስ በመሮጥ የዚያን ሰው ደስታ ያስቡታል፡ ሆኖም ግን ስንቶች የዚህን ታሪካዊ ክስተት ትርጓሜና አመጣጥ በውል እንደሚገነዘቡ መገመቱ ያስቸግር ይሆናል፡ ያ ሰው ግን ስለምን እንደዚያ እንደሚሮጥ በሚገባ ያውቀው ነበር፡ ምክንያቱም በጦርነት የታዳከመ ሰውነቱ ሳይዝል 26ቱን ማይልስ በብቃት ሮጦ እጅግ ታላቅ  የድል ዜናን ለወገኖቹ ካደረሰ በኋላ እስከ ወዲያኛው አርፈዋልና!

ዘመኑ ከክርስቶስ ልደት በፊት 490 ነው፡ ከታላቁ የፐርሽያ (Persian) ኢምፓየር ታላቅና ኃያል ሠራዊት ተንቀሳቀሰ፡ በግዝፈቱም። በታጠቀው መሣሪያ ዘመናዊነትና በስልጠናው ደረጃም የዘመኑ ዓለም ከደረሰበት ዝማኔ በላይ በእጅጉ የረቀቀ ነው፡ በዚህ ላይ ደግሞ ሽንፈትን የማያውቅ የደረሰበትን ሁሉ ጠራርጎ የሚሄድ *"የንጉሦች ንጉስ ። የጌቶቹ ጌታ"* የተባለለት የታላቁ ንጉስ ዳሪዮስ ጦር ነው፡ እናም የቀደመ የድል ታሪኩን እያስታወሰ ታላቅነቱን እያሰበ በኩራት ተንቀሳቅሷል፡ ዓላማው ደግሞ ከወዲያ ያለውን ሉዓላዊ መሬት በሃይል ጨፍልቆ መያዝ ነው፡ ይህ ለንጉሡ ጦር ቀላልና ተራ  ነገር ነው፡ እናም ለውጊያ ስልት የመረጠውን ረባዳውን የመራቶን ሜዳ በቅድሚያ ተቆጣጥሮ ህልሙ የሆነችው የአቴንስ ከተማ ላይ ሆነዋል፡

ከወዲያኛው ግንባር ደግሞ በዚህ ግዙፍ ኃይል እምብዛም ግምት ያልተሰጠውና ግዛቱን ላለማስነጠቅ ብቻ በአራት እጥፍ የሚበልጠውን ታላቁን ጦር የተጋፈጠ የግርክ ሠራዊት ግንባር ግንባር መፋጠጥ ይዘዋል፡ እንዳለመታደል ሆኖ ለክፉ ቀን ተስፋ የተጣለባቸው የጎረቤት እስፓርታ ሰዎች እንኳ ሀይማኖታዊ በዓላቸውን እያከበሩ ስለሆነ ሙሉ ጨረቃ በሰማይ ላይ እስከምትታይ ድረስ ወደ ጦር እንደማይገቡ ምላሽ ሰጥተዋል፡ እናም የቱን ያህል ከባድ ቢመስልም የአቴንስ ሰዎች ሀገራቸውን የመከላከሉን ግዴታ ብቻቸውን ሊሞክሩት ነው፡ ፍጥጫው ለዘጠኝ ቀናት ዘልቋል፡

ቃታውን የሚስብ ደፋር ከሁለቱም ወገን አልተገኘም፡ አንዱ የአቴንሱ የጦር አለቃ "…የሀገርህን ሉዓላዊነትና የትውልዱን ነጻነት አሳልፎ ከመስጠትና እስከወዲያኛው ከመዋጋት የቱ ይሻልሃል?" ሲል ጠጋ ብሎ ጓዱን ጠየቀ፡ ጓዱም አላቅማማም፡ እናም ተስማሙ፡ ቀስት ተሳባ፡ ውጊያው ተጀመረ፡

ጠላትን ግራ በሚያጋባ የውጊያ ስልት የሚታወቁ የታላቁ ኢምፓየር ሰዎች በፍጥነት ሰይፋቸውን መዝዘው ወደፊት ተንደረደሩ፡ ብረት ለብረት ተጋጨ፡ ፉጨቱ እስከ ወዲያኛው የተራራ ጫፍ አስተጋባ፡ የጀግና አንገት ተቀነጠሰ፡ የማራቶን ሜዳ በሰው ሬሳ ንጣፍ ተጓዘጎዘ፡ የማታ-ማታ ፈጽሞ ያልተጠበቀ ክስተት ተሰማ፡

# ስንብት

*የታላቁ ንጉስ ጦር። ያ ሽንፈትን የማያውቅ ኃያል ሠራዊት በሰይፍ እየተመታ ሸሸት ጀመረ፡ የምሥራች ተነገረ - ድል ለአቴንስ ሰዎች ሆነ!*

*ከማራቶኑ ድል በኋላ ያ ታላቁ ኢምፓየር በሕዝቦች ዓመጽ መፈራረስ ያዘ እንጂ ፈጽሞ አልፀናም፡ በዕብሪት ፈረስ እንዳሻቸው መጋለብ የሚሹ ዝንጉዎች በቅሌት እንደሚወድቁ ዜናው እስከ ዓለም ዳርቻ ተናኘ፡ ይህንን ዘመንና ድንበር ተሻጋሪ የሆነ ቁም-ነገር ዓለም ዛሬም በቀጥታም ባይሆን በመራቶን ሩጫ ያስበዋል፡ እርግጥ ነው! ዕብሪትና ብልግና ያልተጠበቀ ውርደትን ያስከትላል፡ 'the sin of hubris' ይሉታል ግርኮች፡*

*ሠሞኑን በኢትዮጵያ ኢምፓየር ዙሪያ እንደተለመደው ዕብሪትና ብልግናን መሠረታቸው ያደረጉ በርካታ ግርግሮችና ዛቻዎች ተስተውለዋል፡ ከሰሞነኛው **የ"ልክ እናስገባችኋለን"** የደንቆሮዎች ድንፋታ እንጀምር፡*

*የሕወሃት ሰዎች የዚህ ዓይነቱን ጦርነት በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሲያውጁ ይህ የመጀመሪያቸው ባይሆንም ምናልባት ግን የመጨረሻቸው ሊሆን ይችላል፡ "**ጦርነትን መስራት እንችልበታለን!"** በሚለው በአቶ ስዩ አብረሃ ዛቻ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የተጀመረው የፀረ-ኦሮሞ ጦርነት በ1992ቱ የወተሩ ጭፍጨፋ ከተረጋገጠ በኋላ። በአቶ መለስ ፊታውራሪነት አድማሱን አስፍቶ ዛሬ ያልገባበት የኦሮሞ ቤት የለም ለማለት ያስደፍራል፡ መሬት ሲቆፈር ከየቦታው እንደዋዛ የሚለቀመው የንጹሃን ዜጎች ዓጽምና በገዛ ሀገሩ ላይ በጥይት ተረሽኖ በአደባበይ የሚሰቀለው ዜጋ የዚህ ዓይነቱ አዋጅ ውጤት ስለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡ **"ፊጻሜው ከወዴት ያደርሰናል?"** የሚለው ቁም-ነገር ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ቢሆንም ይህ ዓይነቱ ግፍ የሚፈጸምበት ሕዝብ ግን መጠነ-ሰፊ አጸፋዊ እርምጃ ለመውሰድ አይገደድም ብሎ መገመቱ ሲበዛ ተላላነት ይሆነል፡ የስንቱ ልብ እየደማ እንደሆነ ማን በነገራቸው!*

*በሌላ በኩል በደራና አዴት መሃከል የተቀሰቀሰው የታሪክ ሽሚያ በወያኔ/ኦህዴድ ጓዳ ዳግም ግርግር ቀስቅሷል፡ **ስንቅና ውሸታም እያደር ይቀላል** እንደሚባለው የኦህዴዶች የምስረታ ታሪክ ለዓመታት ሲነገርለት ከነበረው ከደራ(ኦሮሚያ) ወደ አዴት(ትግራይ) በይፋ መሸኘቱ ለወገኔ ምኑም ባይሆንም በወያኔ/ኢህአዴግ ቤት ግን ገና ብዙ ያልተመዘዙ ካርዶች እንዳሉ ያመለክታል፡ ከዚህም ባሻገር አገልጋዮቹን ለማስደንገጥ ብሎ የሚመዛቸው ካርዶች ገና ከጅምሩ እየተበላሹበት ጨዋታውን ፋርሽ እያደረገበት መሆኑን ያስረግጣል፡*

*እነዚህ በተከታታይ የተደመጡ የልክ ማስገባቱ ዛቻና የደራ/አዴት ጉዳይ ተደማምሮ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሆደ-ባሻነት እየታሙ በሚገኙ አንዳንድ የኦህዴድ ሰዎችና በጦሩ አባላት ዘንድ ኩርፊያ ቢጤ በመፈጠሩ **"ሁሉን ዓቀፍ ዓመፅ ሊያስነሳ ይችላል**' የሚል ስጋት ቀድሞውኑ የፖለቲካ ስሌት ለተጣረሳባቸው ለእነ አቦይ ፀሃዬ ዘመዶች ተጨማሪ የራስ ምታት ሆኗል፡*

*በመሆኑም 'የልክ እናስገባችኋለን!' የብልግና አንደበት የሥርዓቱን መበስበስ ከማረጋገጥ ውጪ ሌላ ውጤት እንደማያመጣ በእርግጠኝነት ሊነገራቸው ይገባል፡ ይህ መሰሉ*

# ስንብት

ትርምስና ግርግር በቀጠለበት ሁኔታ ሌላ የኢምፓየሪቷን አደገኛ አዝማሚያን የሚጠቁም ተጨማሪ ክስተት ከሌላ ጽንፍ ተስተውሏል፥ የአሜሪካ ብሔራዊ የደኅንነት ምክርቤት እጅግ የነጠረ። ያልተዛባና በጥናት የተረጋገጠ ዘገባን ለአሜሪካ የስለላ ተቋማት። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አውጪዎችና ለዓለምዓቀፍ ግንኙነት ተመራማሪዎች በማቀበል ይታወቃል፥ ይህ ተቋም ዘመን ኣስልቶ። ቀን ቆጥሮና በመስረጃ አስደግፎ ኢትዮጵያ ሊጠፉ ከተቃረቡ ሀገራት አንዷ ስለመሆንዋ ግልጽ በሆነ መልኩ አቅርቦ በብዙዎቹ ዘንድ ጠንካራ ትኩረት አግኝቶ ነበር፥

እናም ታዲያ የኦሮሞ ነገር ሁሌም ሕመም የሚሆንባቸው የኢትዮ-አቢሲኒያ ጽንፈኞች ይህንኑ እውነታ በማጣመም ለሕመማቸው ማስታገሻ እንደሆነ ብለው ሠሞኑን ካለው ነባራዊ እውነታ ጋር የሚቃረን ጭብጥ የያዘ ፊልም አሰርተው ሲያሰራጩ ሰንብተዋል፥ የፊልሙ ዋነኛ ትኩረት የኦሮሞ ሕዝብ የነጻነት ትግል ለኣካባቢው ቀጠና ሠላምና መረጋጋት ያለው ሚና ጎልቶ እንዳይታይ፣ እንዲሁም ከተቻለ በሕዝቡ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና መከራ ከዓለም ጆሮና ዓይን በማራቅ ለችግሩ ስልታዊ ከለለን መስጠት ነው፥

ሆኖም ግን ከሀሰት ድራማና ከባዶ አንደበት የሚመነጭ የብልግና ቋንቋ ልትጠፋ ለተቃረበች ኢምፓየር ፈውስ ሊሆን አይችልምና የኢትዮ-አቢሲኒያ ጽንፈኞች ጥረት ኣልሰመረም፥ የደንቆሮዎች ድንፋታና የቀጠፊት ኣንደበት የሕዝቦችን ፊትሃዊ ጥያቄም ሊገታ ኣይችልም፥ ይልቁንም የኢምፓየሪቷን ሊበታትናት ውስጥ-ውጡን እየተንቀለቀለ ያለውን እሳተ-ገሞራ ቢያቀጣጥል ነው እንጂ፥ እያያን ያለነው ሁካታም የዚሁ እውነታ የመጨረሻ የምጥ ጣር ማሳያ ነው፥ ስለዚህም ጥንት በሌሎች ኢምፓየሮች እንደሆነ ሁሉ የጊዜ ጉዳይ እንጂ የኢትዮጵያ ኢምፓየርም በዓይናችን ፊት ትፈራርሳለች፥ ስንብቷም ደመቅ ያለ ይሆናል፥

ይህ ሟርት አልያም ቀልድና ተረትም አይደለም፥ የአንባቢዎቼን ትኩረት ለመሳብ የፈጠርኩት አሉባልታም አይሆንም፥ ግን በእርግጥ ሊሆን ያለ ሀቅ ነው፥ እውነት ነው። ይህ ዓይነቱን ሀቅ መስማት ለአንዳንዶች መራራ ሊሆን እንደሚችልም ኣውቃለሁ፥ ግን ደግሞ መሸፋፈኑ አያዋጣምና ኣይቀሬውን እውነታ ለመናገር ተገደድኩ፥ ከእንግዲህማ እውነትን የማይወድ ወገኛና ነውረኛ ሁላ በቃላት ድንፋታና በሀሰተኛ ፊልም ተከልሎ ወዲያ መሻገር ይከብደዋል፥ ማዕበሉ በሃይል ያራግፈዋልና!

Lakkii na dhiisi siin jennaan na diddee,

Harkuma keetiin barbada haatee of gubdee!

ቸር እንሰንብት!

ጂቱ ለሚ ነኝ